በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ

አሐዱ አምላክ አሜን፡፡

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ... - ክፍል 12

## መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon4@gmail.com

***ቦታ፡-*** ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

ግንቦት ፲፫ ቀን ፳፻፬ ዓ.ም.

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 12

## ቅንነት

- ጌታችን ለሰው ሁሉ ዘወትር ቅን ነው፤ በዚህ ሆነ በወዲያኛው ዓለም በደስታ ለመኖር የሚያስችለን ምን እንደሆነ ያስተምረን ዘንድ ቅን መምህራችን ነው፡፡
- ይህ ቅንነቱም ሰማያዊ ክብሩን ትቶ በፍጹም ትሕትናና ፍቅር ወደኛ ወደምድር ይመጣና መዳንን ይሰጠንና ዘላለማዊ ሕይወትንም ያድለን ዘንድ አብቅቶታል፡፡
- በኃጢአታችን ሆነን ሳለ እንዲወደን፣ ንስሐም ስንገባ ይቅር ሊለንና ኃጢአታችንንም ፈጥኖ በመርሳት ቅዱስ ቁርባን በመቀበል ከርሱ ጋር እንዋሐድ ዘንድ ለመታደል ያበቃን ፍጹም ቅንነቱ ነው፡፡ ‹‹እርሱ አምላክ ነው ሥራውም ፍጹም ነው መንገዱም ሁሉ የቀና ነው፤ የታመነ አምላክ፥ ክፋትም የሌለበት፥ እርሱ እውነተኛና ቅን ነው። ›› ***<u>ዘዳግ 32፡4፡፡</u>***
- እኛም በክርስቶስ በሆነው ትዳራችን እርስ በርሳችን ይህን ቅንነት እናሳይ ዘንድ ይጠብቅብናል፡፡ ‹‹አምላኬ ሆይ፥ ልብን እንድትመረምር፥ ቅንነትንም እንድትወድድ አውቃለሁ›› ***<u>1ኛ ዜና 29፡17፡፡</u>*** ‹‹… ኢዮብ የተባለ አንድ ሰው ነበረ ያም ሰው ፍጹምና ቅን፥ እግዚአብሔርንም የሚፈራ፥ ከክፋትም የራቀ ነበረ።›› ***<u>ኢዮ 1፡1፡፡</u>***
- ጌታችን በዚህም ሆነ በወዲያኛው ዓለም ስለትዳር አጋራችን ደስታ መሟላት በቅንነት እንድንገኝ ይፈልጋል፡፡
- በክርስቶስ አንድ የሆን ባለትዳሮች አንዳችን ለሌላው ታላቅ ኃላፊነት አለብን፤ ለትዳር አጋራችን ቅን መሆን የሚጠበቅብንም ለዚሁ ነው፡፡

# <u>የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 12</u>

## ቅንነት - ለትዳር አጋራችን ፍላጎት መሟላት ቅን ሆኖ መገኘት

- የትዳር አጋራችንን ፍላጎት ለማሟላት እያንዳንዳችን የሚገደን መሆን ያስፈልገናል። እያንዳንዳችንም የትዳር አጋራችን ፍላጎት ምን እንደሆነ አውቀን በሚቻለን ሁሉ ፍላጎቱን/ትዋን የተሟላ ለማድረግ አቅማችን የሚፈቅደውን ሁሉ ጥረት እናድርግ!
- አንዳንድ ሰዎች ማግባታቸው የትዳር አጋራቸው ፍላጎታቸውን ሁሉ እንድታሟላ መልካም አጋጣሚ እንደሆነ ያስባሉ። በሌላ አነጋገር በነርሱ ዘንድ ‹‹ትዳር›› ማለት ‹‹መቀበል›› ነው። በክርስቶስ የሆነው ትዳር እውነታ ግን ‹‹ዘወትር በመስጠት የምንኖርበት›› የመሆኑን እውነታ መረዳት ነው። ‹‹የጻድቃን አሳብ ቅን ነው የኃጥኣን ምክር ግን ተንኰል ነው። … እውነተኛን ነገር የሚናገር ቅን ነገርን ያወራል የሐሰት ምስክር ግን ተንኰልን ያወራል።›› <u>ምሳሌ 12፡5 ፤ 12፡17።</u>

## በክርስቶስ በሆነ ትዳር በቅንነት ሊሟሉ የሚገባቸው አምስት ፍላጎቶች አሉ፡-

1. ሥነ ልቦናዊ ፍላጎት

- ባልም ሆነ ሚስት የትዳር አጋራቸውን ሥነ ልቦናዊ ፍላጎት በንቃት መከታተል ይጠበቅባቸዋል።
- ማንኛውም የሰው ዘር ሁሉ እንዲረዱት፣ እንዲያዝኑለት/እንዲራሩለት፣ ትኩረት እንዲሰጡት፣ እንዲያምኑት፣ በራስ መተማመን እንዲኖረውና አቅርበው ወዳጅ እንዲያደርጉት ይሻል።

# <u>የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 12</u>

1. **ሥነ ልቦናዊ ፍላጎት…**

- የተወደዳችሁ ባለትዳሮች! የትዳር አጋራችን በክርስቶስ በሆነው የተቀደሰ የትዳር ሕይወታችን ፍላጉቱ/ትዋ እንዳልተሟል ሆኖ ከተሰማው/ት ሊጨነቅ/ልትጨነቅ፣ ተስፋ ሊቆርጥ/ልትቆርጥ ይችላል/ትችላለች፤ እግዚአብሔርም ይህን ይመለከትብን ዘንድ አይሻም፤ በትዳር አጋራችን ዘንድ ያለውን ፍላጎት ለማሟላት ጠንክረን መሥራት የሚያስፈልገንም ለዚሁ ነው፡፡

2. **ስሜታዊ ፍላጎት**

- ባለትዳሮች በትዳር አጋራቸው ሊመለከቱት የሚሹት አሥር ስሜታዊ ፍላጎቶች እንዳሉ የተደረሰበት ሲሆን እነዚህም፡- <u>አድናቆት</u>፣ <u>ክብካቤ</u>፣ <u>መነጋገር</u>፣ <u>በቤት በሚያስፈልገን መታገዝ</u>፣ <u>ለቤተሰቡ ኃላፊነት የሚሰማን መሆን</u>፣ <u>የገንዘብ አስተዋጽዖ ማድረግ</u>፣ <u>ታማኝነትና ግልጽነት</u>፣ <u>አካላዊ መስህብ ያለን መሆን (ውበታችንን መጠበቅ)</u>፣ <u>በመዝናናት ጊዜ አብሮ መሆንና</u> <u>የሥጋችን ፍትወት መሟላት</u> ናቸው፡፡
- ከነዚህም ፍላጎቶች አምስቱ በሴቶች ዘንድ ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጣቸው ቢሆኑ በወንዶች ዘንድ ደግሞ ብዙም ትኩረት የማይሰጣቸው ይሆናሉ፡፡ በሁለቱም ጾታዎች ዘንድ ተቃራኒው የሚከሰት መሆኑ የታወቀ ነው፡፡ ከራሳችን ይልቅ ሌላውን ለማስደሰት ከፍ ያለ ጥረት ማድረግ እንደሚያስፈልገው/ጋት በመጽሐፍ የተመከርነውም ለዚሁ ነው፡፡

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 12

3. **ማኅበራዊ ፍላጎት**

- ማንኛውም ሰው ተቀባይነትን ለማግኘትም ሆነ የኔ የሚለው ነገር እንዲኖረው እንዲሁም ክብር እንዲሰጠው ብሎም በራስ መተማመን እንዲኖረው ይሻል፡፡
- የተወደዳችሁ ባለትዳሮች! የትዳር አጋራችን ቀዳሚ ፍላጎት በኛ ዘንድ ተቀባይነትና ሥፍራ ማግኘቱ/ማግኘትዋ ብሎም የራሳችን አድርገን መቁጠራችንን ነው፡፡

4. **አካላዊ ፍላጎት**

- ጌታችን ‹‹አንድ ናቸው እንጂ ሁለት አይደሉም…››› በማለት በሰጠው ትእዛዙ እንደሚታወቀው አካላዊ መፈላለግ በተጋቢዎች ዘንድ የሚገለጥ ፍላጎት ነው፡፡
- አካላዊ መፈላለግ ምስጢረ ተክሊል በተፈጸመበት ዕለት በገቡት የጋብቻ ቃል ኪዳን በተሰጣቸው ትእዛዝ መሠረት በሁለቱም ዘንድ ሊከበር ይገባዋል፡፡
- የተወደድሽ ሚስት ‹‹ ከሚያስፈልገው ሁሉ አታጉድይበት…›› አንተም የተወደድህ ወንድም ሆይ ‹‹… በሚያሻት ሁሉ ከርስዋ ጋር ልትሆን ይገባሃል…››
- ቅዱስ ጳውሎስም ‹‹ሆኖም ከእናንተ ደግሞ እያንዳንዱ የገዛ ሚስቱን እንዲህ እንደ ራሱ አድርጎ ይውደዳት›› *ኤፌ 5፡33፡፡* እንዳለ፡፡

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 12

5. *መንፈሳዊ ፍላጎት*

- ሴት በቅድሚያ የተፈጠረችው ‹‹ሰው ረዳትና አጋር ይኖረው›› ዘንድ እንደመሆኑ መጠን እያንዳንዳቸው ሞራላዊ አቅጣጫቸውን፣ ውስጣዊ መነሳሳትን፣ ፍቅርን፣ እንዲሁም ከጌታችን ከአምላካችን ከክርስቶስ ጋር ሊኖረን የሚገባውን መተሳሰር አስመልክቶ ፣መንፈሳዊ ፍላጎታቸውን በመመርመር እርስ በርስ መተጋገዝ ይኖርባቸዋል፡፡
- በክርስቶስ የሆነ ትዳር ዋና ግቡ በክርስቶስ መኖር ነው፡፡ በዚህም የተነሳ ተጋቢዎቹ ይህንን ታላቅ ግብ ለመምታት ከጌታችንም ሆነ እርስ በርሳቸው ቀጣይነት ባለው መተሳሰር በአንድነት መኖር ያስፈልጋቸዋል፡፡
- ‹‹በቅንነት የሚሄድ ይድናል በጠማምነት የሚሄድ ግን ወዲያው ይወድቃል፡፡›› *ምሳ 28፡18፡*
- ‹‹እግዚአብሔር ከመሥዋዕት ይልቅ ጽድቅንና ቅን ነገርን ማድረግ ይወድዳል፡፡›› *ምሳ 21፡3፡፡* ‹‹በቅንነት የሄደ በአልጋው ላይ ያርፋል፡፡›› *ኢሳ 57፡2፡፡*
- ‹‹የእውነትን ቃል በቅንነት የሚናገር የማያሳፍርም ሠራተኛ ሆነህ፥ የተፈተነውን ራስህን ለእግዚአብሔር ልታቀርብ ትጋ፡፡›› *ካል ጢሞ 2፡15፡፡*
- ‹‹ወዳጆች ሆይ፥ አሁን የምጽፍላችሁ መልእክት ይህች ሁለተኛይቱ ናት፡፡ በቅዱሳን ነቢያትም ቀድሞ የተባለውን ቃል በሐዋርያቶቻች ሁም ያገኛችኂትን የጌታንና የመድኃኒትን ትእዛዝ እንድታስቡ በሁለቱ እያሳሰብኂችሁ ቅን ልቡናችሁን አነቃቃለሁ፡፡ ›› *ካል ጴጥ 3፡1-2፡፡*

ታማኝነት

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 12

- ታማኝነት ከልጅነት ጀምሮ የምናዳብረው ሕይወት ሲሆን ዕድሜያችን እየጨመረም ሲሄድ አብሮ የሚያድግ ነው፡፡
- እያንዳንዳችን ለእግዚአብሔርና ለቤተ ክርስቲያኖች ታማኝ መሆን ይኖርብናል፡፡
- በመቀጠልም ለወላጆቻችን፣ ለባልንጀሮቻችን፣ ለአገራችን፣ ለቃል ኪዳናችንና ለእምነታችን ታማኝ መሆን ይጠበቅብናል፡፡
- በክርስቶስ በሆነ ትዳር የሚኖሩ ተጋቢዎች ዕድሜ ልካቸውን አንዳቸው ለሌላው ታማኝ ሆነው የሚኖሩበት ሕይወት ነው፡፡ ‹‹አንተ በጎ ታማኝም ባሪያ፤ በጥቂቱ ታምነሃል፥ በብዙ እሾምሃለሁ፤ ወደ ጌታህ ደስታ ግባ አለው፡፡›› *ማቴ 25፡21፣ ሰቆ ኤር 3፡23፡፡*
- ነገሮች ሁሉ መልካም ሆነው ሲገኙ ታማኝነት ከባድ ባይሆንም ችግሮች ሲፈጠሩ ግን ፈተናዎች መፈጠራቸው አይቀርም፡፡ ስለዚህ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ራሳችንን መጠየቅ ያስፈልገናል፡- **ባል ወይም ሚስት፡-**
  - *በሕይወት ጫና/በጭንቀት ቢዋጡ፣ ቢታመሙ ወይም ከፍተኛ ችግር ውስጥ ቢዘፈቁ*
  - *አንዳንድ ጊዜ ፍቅራቸውንና ርኅራኄያቸውን አጥፍተው ግትር ወይም ክፉ ቢሆኑ*
  - *ግኑኝነታችን በሚያበሳጭና አሰልቺ በሆነ ግኑኝነት ሥር ሲወድቅ ወይም*
  - *በኛ ፈንታ ሌላው ሰርጎ በመግባት ለማባለግ የሚያስችል ክፍተት ሲፈጥር/ስትፈጥር*

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 12

## ታማኝነት

- *የትዳር አጋራችን ፍቅሩን/ፍቅርዋን መግለጡን/መግለጥዋን ሲያቆም/ስታቆም*
- *ረጅም ጊዜ ባስቆጠረው ትዳራችን እኛ ብዙ መሻሻል ስናደርግ ሌላው ግን በሥራም ሆነ በሌላው መስክ ምንም ዓይነት መሻሻል የሌለበት ሲሆን*
- *በርካታ ሰዎች ምን ያህል አስተዋይ፣፣ ብልህና ለየት ያልን ሰዎች እንደሆን ሲገልጡልን የትዳር አጋራችን አድናቆቱን/አድናቆትዋን የማይገልጥ/የማትገልጠው ሲሆን*
- *አንተ/እርስዋ የርሱን/የርስዋን ፍላጎት ለማሟላት ከመድከማችሁ በቀር የትዳር አጋራችን ለፍላጎታችን መልስ የማይሰጥ/የማትሰጥ ሆኖ/ሆና ሲሰማን*
- *የትዳር አጋራችን በኛ መደሰቱን/መደሰትዋን ትቶ/ትታ የራሱን/የራስዋን ደስታ ብቻ ለማሟላት ሲጣደፍ/ስትጣደፍ ስናይ*
- *የትዳር አጋራችን እምነታችንን በሚጋፋ መልኩ በኛ ላይ ክህደት ሲፈጽሙ **ለትዳር አጋራችን በታማኝነታችን መቀጠል እንችላለን?***
- ከላይ ለተጠቀሱት ጥያቄዎች ጤናማ ምላሾች መስጠች ካልቻልን ለትዳራችን ባለን ታማኝነት ዙሪያ ራሳችንን መልሰን መመርመር ያስፈልገናል። ከሁሉም በላይ ተገቢ ባልሆነ መልክ ምላሽ የሰጠንባቸው ጉዳዮች ሊሻሻሉ የሚችሉና መሻሻልም የሚያስፈልጋቸው እንደሆኑ እናስተውል!
- ከሁሉም በላይ ልናስታውሰው የሚገባን እውነት አምላካችን ክርስቶስ በግኑኝነታችን መካከል ያለ መሆኑን ነው።
- ምናልባት ለትዳር አጋር ያለመታመን መብት እንዳለን ቢሰማን ይህ አለመታመን ለትዳር አጋራችን ብቻ ሳይሆን ለጌታችን ለአምላካችን ለኢየሱስ ክርስቶስም ያጎደልነው መታመን እንደሆነ እናስተውል!!!

# ይቆየን።

For your queries or questions E-mail:
kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :
www.zeorthodox.org